# እንዳትፀፀትብኝ

ማፍቀር መውደድህን በቃልህ አስረዳኝ፤
አሳቢ እረዳቴ መሆንህን በተግባር አሳየኝ፤
ያለኝ ጊዜ ቀርበህ ሳጣ አትራቀኝ፤
በሁሉ ተግባርህ ግልፅ ሁንና ጉድለቴን ንገረኝ፤
አለመኖሬን አይተህ ለማንም አትማኝ፤
የምትስመኝ መስለህ ይዘህ አተንክሰኝ፤
የምትስበኝ መስለህም አትገፍትረኝ፡፡

ፍቅር ካለህ ለኔ በሕይወት እያለሁ በተግባር አሳየኝ፤
ስጠማ ስራብ ያለህን አካፍለኝ፤
ተራቁቼም ካየህ እንዳላየ አትለፈኝ፤
መላው ሲጠፋብኝ ግራም ስጋባም እጄን ይዘህ ምራኝ፤
የደስታዬም ጊዜ ተገኝተህ ተካፋይ ሁንልኝ፤
ከዚች የሩጫ ዓለም ድንገት ከተሰናበትኩኝ፤
አደራ ጓዴ ሆይ እንዳትፀፀትብኝ፡፡

በሕይወት እያለሁ በሌት ተቀን ተግባርህ አስደስተኸኛል፤
ኑሮ ትርጉም ሲያጣ ደግፈህ ተንከባክበኸኛል፤
በፀሐይም በብርዱም ሳትለየኝ አብረኸኝ ተንከራተሀል፤
በሀዘኔም በደስታዬም ዘወትር ተካፋይ ሆነሀል፤
በዚህ ሁሉ ተግባርህ የሞቀ የፍቅር ጎጆ እልቤ ሰርተሃል፤
ታዲያ ብለይህስ እንዴት ይከፋሃል፤
ፍቅርህ ለመኝታዬ ድልዳሌ ሆኖኛል፤
ደግነትህም ልባሴ ከብርዱ ይከላከለኛል፤
ምስጥ ሥራዬን ቢበላው ፍቅርህ ለዘላለም ከኔ ጋር ይቆያል፡፡

ከ ኒኒ ለገሰ